# ይህንን ቁጭታዊ ግጥም፤ ገፋፍቶ ያስገጠመኝ፤ ምክንያታዊ መንስኤ...

## (ገሞራው - ምድረ ስዊድን)

ዘንድሮም እንደወትሮው የተፈፀሙ አረመኔያዊ ትግብርቶች፤ በቀጥታ ካለሁበት ገጭ ብለው መጥተው፤ እኔኑ ያንገላቱኝ ያህል ተሰምተውኛል፡፡ ሁለቱን ልጥቀስ፡፡ ከህፃንነት እስከ ጉልምስና እድሜዬ ከኖርኩበት ደብረ ሰላም(ሰላም አምባ) ቅዱስ እስጢፋኖስ ቤተክርስቲያን አደባባይ፤ የሰማእቱ እስተ-ሞት በሚታሰብበት በአል ላይ ታቦቱ ለኡደት ወጥቶ እንዳለ፤ አንድ አረጋዊ አባት (ባህታዊ ፈቃደሥላሴ) በጥይት ተቀጥቅጠው አልፈዋል፤፤ ያ አይነቱ የአደባባይ አረመኔያዊ ግድያ በይዘቱም ሆነ በአይነቱ ላካባቢው ታሪክ የመጀመሪያ ነው፡፡

ለዘመናት በሰላም የኖሩ ባይሆኑም፤ የደብሩ ካህናት ወገኖቼ ድርጊቱ እየዘገነናቸው ዛሬም የሚነዝራቸው መሆኑን ሰምቼ እጅግ አዝኛለሁ፡፡ የኛ አረጋዊ አባት ንፁህ ደም ከፈሰሰበት ላይ ገና ሳይደርቅ፣ በቅርቡ ደግሞ የቅርብ ወንድሜ የሆነው ጀግናው አሰፋ ማሩ በጊዜው ከመኖሪያ ቤቱ ላይ በተመሳሳይ አሰቃቂ ሁኔታ፣ በጥይት ተደብድቦ አልፋል፡፡ "እማኝ" በተሰኘ ወርሃዊ መጽሄቱ እኔን በሚመለከት የፃፋቸውን ያነበበ ሁሉ፤ የሱ መገደል፤ ምን ያህሉን የኔን ህልውና እንዳበሳጨና እንዳበገነ፤ ሊረዳልኝ ይችላል ብዬ አምናለሁ፡፡

ወንድሜ አሰፋ በነጠረ መንፈስ የሚታገል ሊቅ እንጅ፣ አረመኔዎች ገዳዮቹ እንደፖለተኩት፣ እንደራሳቸው፣በግብዝ ጡንቸኛነት አምኖ፣ በባሩድ ጭስ የሚያፍን ሰው አልነበረም፡፡ ሁለቱም የአረመኔዎች ሰለባ ሆነው የወደቁት ወገኖቼ፣ በአካለ ሥጋ ይለዩኝ እንጅ፤ ምንጊዜም በመንፈስ ከኔው ጋር ናቸው፡፡ በሞትና በህይወት መካከል ያለውን የመንፈስ አንድነታችንን፣ ለቀሚ ሰው

ለማዘከርና ለማስታወስ፣ ተከታዩን የቁጭት መግለጫ ግጥም፣ ለሃዘኔ ማፅናኛ እንዲሆን ጭምር፣ አቅርቤአለሁ፣፣

## ......ብሆንማ ኖሮ!

### ( ስላልሆንኩ ሳተ እንጅ!!! )

በስጋና በአጥንት - በደምና በፀጉር - በጥፍርና ጅማት - ተገንባሁ እንጅ!

ዝም አልልም ነበር - ከመጠኑ አልፎ - ያ ግፍ ሲደረጅ፣

ንፁሀኑን ወገን - አድብቶ ሲፈጅ

ወሮው ሲያንገላታ - ሲያምስ ሲቀጠቅጥ - ሲነዳ ባዋጅ፣

መች ያስችለኝ ነበር - ሰውን ያህል ፍጡር - ባደባባይ ሲገድል - አውሬው

- የሰው ልጅ፣፣

አልሆንኩኝም እንጅ - ብሆንማ ኖሮ!

የሰማዩን መብረቅ - ባለሳት ወደሮ፣

እሰቅለው ነበረ - ከራማ አንጠልጥዬ - ያን የሰው ክርክሮ

በእርግጥ አይቀር ነበር - እንዲህ አንጀቴ አሮ !

በርግጥ ብሆን ኖሮ - የሰማዩን መብረቅ፤

አነደው ነበረ - ካለበት ገብቼ - ያንን ነፍሰ ገዳይ - በንፁሀኖች ደም-

-እንዲያ ሲጨማለቅ

ተምዘግዝጌ ሄጄ - ከዚህ ምድር ጥጋት - ባክናፈ ደመናት - ባየር ሰንደቀደቅ

አሳየው ነበረ - ያን የሴጌዎን ቁራጭ፣ የሰው ነፍስ አዋክቦ፣ አጉል ሲመፃደቅ

ብሆንማ ኖሮ - የአራዊት ነጎድጓድ፤

አደነቁር ነበር - በጆሮ ግንዱ ላይ፣ ማእበል ለቅቄ፣ አጡዞ እሚያሳብድ፣፣

አይደለሁም እንጂ፣ ብሆንማ ኖሮ - ያንን አውሎ ነፋስ!

አሳየው ነበረ ፤ ያንን ነፍሰ ገዳይ - የራሱን አሙዋሙዋት በደምመላሽ፣ ደንደስ!

እመቀ እመቃት አውርጄ ስከተው፤ ከዚያ አንጦርጦስ!

ገያ እንደሰበረው፤ ማሽላ ጠባቂ፤

ማማ ላይ ተሰቅሎ፣ እንደሚያስፈራራው እንዲያ ወግ ጠራቂ፤

አሸመድምጄው ነበር - ገና ያኔ ድሮ፤ ብሆንማ ኖሮ - መልአክ ሰው አዋቂ!

ብሆንማ ኖሮ - የአየራት ነጎድጓድ ፤ ከሰማይ የሚበርቅ፤

ስንቱን እኩይ ነበር - የማስገባው ድባቅ ፣

ቀጥቅጨ ቀጥቅጨ - ጎልጎታ አውርጄ፤ የምከተው እመቅ፣

ካፈር ከትበያው ጋር - ባንዴ እማደባልቅ ፣

ሳልሆን ቀረሁ እንጂ - የሰማይ ነጎድጓድ፣

ስንቱን እቡይ ነበር - እቃጥዬ እማነድ፣

ብን ትን አድርጌ - የማወርድ ምድረ ፋይድ፤

ብሆንማ ኖሮ - የዚያን ነሐሴ ዶፍ፣

የጳጉሜን ፋፋቴ - የክረምቱንም ጎርፍ፣

ስንቱን አረመኔ - በሰው እሚጫወት፣ በደባና በግፍ፣

ጠራርጌ ሁሉን - በርባሮስ አውርጄ፤ ከዚያ አንጦርጦስ፣ ነበረ መዘፍዘፍ

በትሬንታ ጭኜ - ያንን ሁሉ ባንዳ ፣ ጠቅልዬ ወስጄ፤ ነበር የማራግፍ ፣፣

እንዲያው ሳላስበው - ሰው ሆኖ ፍጥረቴ፣

የንብ ያህል እንካ - የመርዝ ጠብታ፣ ሳይኖረኝ ሳላገኝ፣ እንዲያ በማጣቴ፣

ልዩ ሜካኒዝም - የሌለው ሆነና፣ ማጥቃት መከላከል፣ የሰው ሰውነቴ፣

እንዳረረ አለ - በንዴት ተቃጥሎ፣ ውስጣዊው አንጀቴ፣

ዋናዎቹ ክፍሎች - ያካል የገላዬ፣ ልቤ ኩላሊቴ፣ ሳምባዬና ቆሽቴ ፣፣

ብሆንማ ኖሮ - የጢስ አባይን ጎርፍ ፣ ጥርህርሁን የሚያፍስ ፣

አሳየው ነበረ - ጠራርጌ ካገር፣ አፍኜ ወስጄ፣ የምጥል በርባሮስ፣

ከናዝሬል ጉድጓድ - ከነአዛዝሄል፤ ተባይና ቅንቅን፣ በመፍላት ካለበት፣ ከዚያ ካንጦርጦስ፣፣

አይደለሁም እንጅ - ብሆንማ ኖሮ፣ የጳጉሜን አፈና፣

አሳየው ነበር - ያንን ሁሉ ባንዳ፣ እሴቱን ለክቼ፣ ዋጋውን መዝኜ፣ ለስራው ሙስና፣

እንዲህ እንዳሾፈ - መቼ ይቆይ ነበር፣ ነፍሰ ገዳይ ሁሉ ፣ ሰክሮ በጭቆና፣

ሞጥማጣ ሞጥማጣ - የሰው ልጅ ምንነት፣ ክቡር ቅዱስ ፍጡር፣ መሆኑ እማይገባው ደንቆሮ ነውና ፣፣

አይደለሁም እንጅ ብሆንማ ኖሮ - ነደ ነበልባሉን፣ የሳቱን ኮረንቲ፣

አንቸስችሼ እንድጄ - ጠብሼ ቀቅዬ፣ አተን አበን ነበር ግፈኛውን መልቲ!

በዚያው ባደባባይ - በጥይት ቀጥቅጦ፣ በሾተሉ አርዶ፣ ንፁሃን ወገንን፣ ባጠፋበት

ቦታ፣ እሰጠው ነበረ፣ በዚያው ባደባባይ ዋጋውን ላላቲ

አልሆንኩኝም እንጅ - ብሆንማ ኖሮ፣ አንዳጅ አቃጣዩን፣ ቤንዚን አለያም ጋዝ

ወይም ክብረ ሰማይ - ሥጋ ውስጥ ገብቼ፣ ነፍስ እምጠዘጥዝ፣

አለያም ያንን ድኝ - ካጥንት ጉልጥምት ገብቶ፣ ስር እሚያደነዝዝ፣

ብሆንማ ኖሮ - ከልብ ስር ገብቶ፣ እንደበታች አሲድ፣ ነፍስ -

የሚያቅነዘንዝ

አለዚያም ያንን መርዝ ፣ እሰጠው ነበረ- ተመጣጣኝ ዋጋ ላጠፋቸው

ነፍሶች ለፈፀመው መዘዝ !!

አይደለሁም እንጅ - ያንን ምህረት የለሽ፣ ነፍስ አውልቅ መጋኛ፣

ንፁሃንን ገድሎ - አረመኔው ባንዳ፣ መች ይችል ነበር፣ አንዲት

ሰአት እንካ ፀጉሩን አንጨፍርሮ፣ ተዝናንቶ እሚተኛ!!!

በጀው እንጅ ለሱ - እኔ አለመሆኔ፣ አሳልፎ ሰጭ፣ ወይ እንደ ይሁዳ ወይ

እንደጲላጦስ

ገና ድሮ ነበር - ለሰራቸው ግፎች፣ ዋጋውን የምከፍል፣ ለተጫወተበት

በንፁሃኖች ነፍስ፤፤

አለመሆኔማ - ለሱ በጀው እንጅ፣ ብሆንማ ሮኬት፣

አደባየው ነበር - የዘር ዘሩ እንዳይተርፍ፣ በታትኜ ካዘቅት፣

እስከዘላለሙ-ድምጥማጡ ጠፍቶ በንፁሃን ወገን ዳግም ላይጫወት፤፤

አይደለሁም እንጅ - ብሆንማ ኖሮ ፣ ሳታላይት የሰማይ ፣

አሳየውም ነበር - ተምዘግዝጌ ሄጄ ፣ ከዚህ ካለሁበት ፤ ከምድሩ ጥጋት ላይ

ትቢያ አመድ አድርጌ- ስቆጋው ስወቃው፤ ትናኝ ቡናኝ ሆኖ፣ በይፋ እንዲታይ

ከመቅፅበተ አይን - ኢምንት ወደጋመድ፣ ሆኖ ሲደመሰስ ምንም ሳይቀር ላዋይ፣

አለመሆኔማ - በጅጉ ጠቀመው፣ የሚጣቁን ጠበል፣
አሳየው ነበረ - ጋኔኑን አግዝፌ፣ በየአረሁ ላይ፣ ዋይ ዋይ እያሰኘሁ፣
ሳስጮኸው የምውል!!

ብሆንማ ኖሮ - ባለእሳቱን ሰይፍ፣ ወይ እንደ ገብርኤል አለያም ሚካኤል፣
ነበልባሉን እቶን - በሚተፋው ጦሩ፣በፍህመ አለንጋው፣አኮማትሮ እሚገል
ካሉበት ገብቼ - ከተሸሸጉበት፣ ከግፍ ምሽጋቸው፣ ሰራዊት ሳጥናኤል፣
የባንዳ መንጋዎች- ምድረ ጭራቅ ሆነ፣ ጋኔል ወለጌዎን፣ የውሻ ግፈኞች፣
አይቀልዱም ነበር ፣ እንዲያ በሰው ህይወት፤ በሥላሴ አምሳል!!!

እንደዚያ ሚጥሚጣ፣ ውስጣዊ አካላትን፤ ሰርስሮ እሚያናውዝ፣
ጠቅላይ ቢሮ ገብቶ፣ ነርቭ እሚወዘውዝ ፣
ምሱን እሰጥ ነበር - ዘረኛውን ገዳይ ፣ ሆኜ ባደባባይ አፍዝ ወአደንግዝ ፣፣
ሆኜ ብሆን ኖሮ - ያንን መድፍን ፀር፣ የምድር የሰማያት፣
ባገር የገባውን - ዘረኛ ወረርሽኝ፣ ኔፍሊም መናፍስት፣
እንደተነገረው - በኦሪት ዘፍጥረት፣ አለም እንዳጠፉት፣
በየብስ በአየሩ -ተረጭተው ተዋልደው፣ በሆኑት መላእክት፣ልቡሳነ አጋንንት
በደመሰስኩ ነበር - ላንዴም ለምን ጊዜም፣ ድራሹን አጥፍቼ፣ ገሃነም የምከት
ብሆንማ ኖሮ -ዲዲቲ ቢኪኒ ፀረ ነፍሳት ቅመም ፣
ከበረሃ ፈልቶ - ከተማ ውስጥ ገብቶ፣ ብዙሃን ካሉበት፣ ጤና የነሳውን፣
ቢምቢና፣ በረሮ፣ ባንድነት ለማውደም
አልተኛም ነበረ - መርዤ ለማጥፋት፣ ቀን ሆነ ሌሊትም፣፣

አይደለሁም እንጂ - ብሆንማ ኖሮ፣ ቲኤንቲ አሲድ፣
ባንተከተኩ ነበር-እንደነፍር ውሃ አካሉን ለማድረግ፣ብናኝ ብትን አመድ
አይደለሁም እንጅ- ብሆንማ ኖሮ መዳመጫ ሩሎ
ወይም የጣልያኑን - ትልቁን ካባዱን፣ ግዙፉን አሎሎ፣

አሳየው ነበረ - ያንን ነፍሰ ገዳይ፣ ከስር አጋድሜ፣ እንደቸርችል
አስፋልት፣ ካፈር አጣግቼ፣ አድርጌ አመልማሎ፣
አይደለሁም እንጅ - ብሆንማ ኖሮ፣ መድፍና መትረየስ፣
ኢላማዬ ነበር - ያ ጨካኙ ባንዳ፣ ውሻ ነፍሰ ገዳይ፣ ባንዴ እንዲደመሰስ
አይደለሁም እንጅ - ብሆንማ ኖሮ፣ የሪሞቱ ፈንጂ፣
ስንቶቹን ንፁሃን - አስሮና አፍኖ፣ በጭከና ገድሎ፣ አይኖራትም ነበር፣
ራሱም ታፍኖ፣ ይሞታታል እንጅ!
ብትንትኑ ወጥቶ ሥጋና አጥንቱ፣ ለቀብር እንዳይመች፣ ላፈር
እንዳይበጅ፣፣
ብሆንማ ኖሮ - የባህር ውቅያኖስ፣ ደምሳሹን ማእበል፣
አንገላታው ነበር - እሱ እንዳንገላታው፣ የዋሁን ወገኔን ባልፈፀመው ወንጀል!!
ብሆንማ ኖሮ - የፋመ የጋመ፣ ነበልባለ እሳት፣
እፈጀው ነበረ - እያንዳንዱን ገዳይ፣ ፈልጌ ካለበት፣
ተደብቆም ቢሄድ - ከገባበት ምሽግ፣ እከውነው ነበር በየደረሰበት!!
አይደለሁም እንጅ - ብሆንማ ኖሮ፣ ሰይፍና ጎራዴ፣
ባጠፋሁት ነበር - ቀንጥሼ ቆርጬ፣ ከትፌ መትሬ፣ ላዋይም ሳላስቀር፣ ያንን
ነፍሰ ገዳይ፣ ሺ ጊዜ ጊዜያት፣ እንዴት ለምን አንዴ!!!
አይደለሁም እንጅ - ብሆንማ ኖሮ፣ ያንን ድንጋይ ወፍጮ፣
እሰልቀው ነበር - ነፍሱን ከስጋው ጋር፣ ባንድነት እንዲልም፣ እንደ ቸሃ ቆጮ
እንዲያ አለመሆኔ- በጀውና ዛሬ ፣
እንዳሾፈ አለ - በነፍሳት ሲጫወት፣ የሚያጠፋው ጠፍቶ፣ ዘረኛው አጅሬ!!...

ምንጭ

ገሞራው (ኃይሉ ገብረ - ዮሐንስ ) ( 1989 ዓ.ም.)። *ቋሜታዊ ግጥም*። ስዊድን፤
ኢትዮጵያዊነት። (ቅጽ 1፣ ቁጥር 1)